# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

**ተዛማጅ ደምቦችና መመሪያዎች፡-** ACA, ACF-RA, ACH, ACH-RA, COA, COA-RA, COC-RA, COE-RA, COF-RA, COG-RA, EBA-RA, EBJ-RA, EBK-RA, ECC-RA, EEA-RA, EKA-RA, GKA-RA, IGN, IGO-RA, JGA-RA, JGB-RA, JHC, JHC-RA, JHF-RA, JHG-RA, JPD, JPD-RB, በድርድር የተከናወኑ የማሻሻያ ስምምነቶች

**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** Deputy Superintendent; Chief Operating Officer; Chief of School Support and Well-being; Chief of District Operations; Chief of Human Resources and Development; Chief of Strategic Initiatives

## ወንጀል፣ አደጋ፣ ጥቃት ወዘተ. የመሳሰለ ከባድ ኩነት ሪፖርት ማድረግ

I. **ዓላማ**

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የት/ቤቶች ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ (OSSWB)፣ የሰው ሃብት ልማት ቢሮ (OHRD)፣ የትምህርት ተቋማት ደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት (DSSEM) እንዲሁም ለሌሎች የ MCPS ቢሮዎች፣ የህግ አስከባሪ አካላት እና ሌሎች የውጭ ኤጀንሲዎች የደህንነት ጉዳዮችን ሪፖርት ስለማድረግ መመሪያ ለመስጠት።

በተቀናጀ/ሲነርጂ ወይም ሌሎች የሪፖርት ፕሮቶኮሎችን በመጠቀም የትምህርት ተቋም ምላሾችን ለማስተባበር እና ለመምራት

እንደነዚህ አይነት ክስተቶችን በአግባቡ ለሕዝብ ሪፖርት ስለሚደረግበት ሁኔታ መመሪያ ለመስጠት

II. **ትርጓሜ**

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት ማንኛውም በ MCPS ባለቤትነት የሚመራ ወይም የሚተዳደር ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተቋም፣ የ MCPS አውቶቡሶች እና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች፣ንብረቶች/ፋሲሊቲዎች እና/ወይም ማንኛውም ተማሪዎችን በማሳተፍ በ MCPS የሚደገፍ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት መሬትና ግቢን ይጨምራል።

B. ርእሰ መምህር/ዳይሬክተር ማለት እንደአስፈላጊነቱ ለት/ቤት ወይም ለቢሮ ወይም ለሚወክሉት ተቋም ሀላፊነት ያለው አስተዳዳሪ ነው።

C. መዘገብ ያለበት ክስተት ማለት ማንኛውም—

1. በ MCPS ንብረት ላይ ወይም ት/ቤት ስፖንሰር ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ጋር ታያያዥ ሆነው የተከሰቱ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ሪፖርት የተደረገ ክስተት፣ እና

2. በሰራተኞች ወይም በተማሪዎች ላይ በተወሰነ ደረጃ አደጋ፣ ጉዳት ማድረስ ወይም ለጉዳት የሚዳርግ ማስፈራሪያ፣ ወይም የትምህርት ቤት ስራዎችን በእጅጉ የሚረብሽ ከሆነ፣ ወይም

3. ሰራተኞችን ወይም ተማሪዎችን የሚመለከት/የሚያሰጋ እና ለማህበረሰቡ አስጊ የሆነ ወይም ፖሊስ ጣልቃ መግባት ያለበት ከፍ ያለ ህግ የተጣሰበት ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

## III. የኩነቶች/የክስተቶች ምላሽ አፈጻጸም

### A. የፈጣን ክስተት ምላሽ

ከትምህርት ሰዓት/ቀን በፊት ወይም በኋላ የሚከሰቱትን ጨምሮ፣ ሪፖርት መደረግ ያለበት ሁኔታ ሲከሰት፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች በተዘጋጀው የት/ቤት ቀውስ ሁኔታን የመግታት እቅድ መሰረት ድንገተኛ ሁኔታውን መፍታት አለባቸው፣ ጉዳዩንም ወዲያውኑ ለርእሰመምህራቸው/ዳይሬክተራቸው ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

1. ሰራተኞቹ ተገቢውን ቀጣይ ግንኙነት በሚከተለው መልኩ ያከናውናሉ፡-

    a) ማንኛውም 911 የአደጋ ጊዜ ጥሪ ከተደረገ በኋላ፣ ርእሰመምህሩ/ዳይሬክተሩ ወይም ተወካይ ሥርአት አቀፍ የትምህርት ተቋማት የደህንነት መምሪያን/Department of Systemwide Safety and Security (DSSEM) ያነጋግራሉ፣ መምሪያው በዋና ቢሮ የአደጋ መከላከል ስምሪት ዝርዝር ላይ በተገለፀው መሠረት መደረግ ያለበትን ግንኙነት ያስተባብራል።

    b) 911 የአደጋ ጊዜ ጥሪ የማያስፈልጋቸው ክስተቶችን ወዲያውኑ ወደ OSSWB ሪፖርት መደረግ አለባቸው፥ ወይም ዲስትሪክት አቀፍ የአስቸኳይ/የአደጋ ክስተት ቡድንን ማሠማራት እና በዋናው ቢሮ የመከላከል ዝርዝር ውስጥ ያሉትን የግንኙነት መስተጋብሮች እንዲያስተባብር እንደአስፈላጊነቱ ድንገተኛ ሁኔታው/አደጋው በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሪፖርት መደረግ አለበት።

    c) በት/ቤት ቅፅ 236-2 የድንገተኛ አደጋ መከላከል እቅድ የትምህርት ቤት የድንገተኛ አደጋ እቅድ ላይ ወደ DSSEM ወይም OSSWB የመደወል ሀላፊነት ያለው ሰራተኛ መሰየም አለበት።

2. አንድ ክስተት ከትምህርት ሰዓት በፊት ወይም በኋላ (ለምሳሌ፡- ትምህርት ቤት ማቋረጥ ወይም በሳምንት መጨረሻ ላይ የህዝብ ንብረትን ያለምክንያት ማውደም/ማበላሸት) ከተከሰተ እና ወደ DSSEM እና/ወይም ለርእሰመምህር ሪፖርት ከተደረገ፥ DSSEM ሰራተኞች እና ርእሰ መምህሩ ወዲያውኑ OSSWB ማነጋገር አለባቸው።

3. እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀጥታ ለሚመለከታቸው ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ያሳውቃሉ።

    a) ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና ለሠፊዉ ህብረተሰብ ማሳወቅን በተመለከተ ከዚህ በታች ሰክሽን V ይመልከቱ።

    b) MCPS ደንብ JHC-RA ላይ እንደተደነገገው፣ የልጅ መጎሳቆል እና ቸልተኝነት ጥቃትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ፣ የተጠረጠሩ የልጅ መጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ሁኔታዎችን ለወላጆች/ሞግዚቶች በማን አማካይነት ማሳወቅ እንደሚገባ ለመወሰን ርዕሰመምህራን/ተወካዮች ከህግ አስከባሪዎች ጋር መተባበር አለባቸው።

B. የማህበረሰብ ተሳትፎ ኦፊሰሮች (MOU-CEO) የመግባቢያ ስምምነት መሰረት፣[1] የሚከተሉት ክስተቶች ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ እና DSSEM ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው።

1. ተገቢው የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ለሚከተሉት ምላሽ ለመስጠት እና ለመመርመር ሃላፊነት በመውሰድ በግንባር ቀደምትነት ይሠራል -

a) ሞት (ራስን ማጥፋት ወይም ራስን የማጥፋት ሙከራን ጨምሮ፣ ራስን የማጥፋት አደጋ ስጋት፣ MCPS ቅጽ 335-54 ራስን የማጥፋት አደጋ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ) ይመልከቱ.

b) አስገድዶ መድፈር እና/ወይም ስምምነት የሌለው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ድርጊት ወይም ግንኙነት (የተጠረጠረ የሕፃናት ጥቃት እና/ወይም ቸልተኝነት፣ MCPS ደንብ JHC-RA፣ የሕፃናት ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና መመርመርን ይመልከቱ)።

c) ዘረፋ/የዘረፋ ሙከራ (አጥፊው የታጠቀም ሆነ ያልታጠቀ፥ የሌላውን ንብረት ከግለሰብ ነጥቆ መውሰድ ወይም ባለቤት በተገኘበት በኃይል መውሰድ፣ የሆነ የአመፅ ስጋት/ፍርሃት መፍጠር፣ ወይም ማስፈራራት)።

d) የጥላቻ ወንጀል (ማንኛውንም ወንጀል መፈጸም፣ ሰውን ማዋከብ ወይም የሰውን ንብረት ማበላሸት፣ በተጠቂው ዘር፣ ቀለም፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ሃይማኖታዊ እምነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ ቤት አልባነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት የሚፈፀም የወንጀል ድርጊት)።

e) የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት፣ እያወቁ ወደ ትምህርት ቤት ንብረት ይዞ መምጣት ወይም መታጠቅ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ አደገኛ ወይም ገዳይ መሳሪያ መጠቀም፣ በማንኛውም ፕሮጀክት ላይ ጉዳት ለማድረስ የተቃጣ ወይም የተተኮሰ መሳሪያን ጨምሮ (በተጨማሪ MCPS ደንብ COE-RA፣ ይመልከቱ) የጦር መሣሪያ)።

f) ከወንበዴዎች ጋር የተያያዘ ክስተት/ወንጀል (በተጨማሪ MCPS ደንብ JHG-RA፣ የወንበዴዎች፣ የወሮበሎች ቡድን እንቅስቃሴ፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አጥፊ ወይም ህገወጥ የቡድን ድርጊት/ባህሪ መከላከል ይመልከቱ)።

2. ከርእሰ መምህሩ/ዳይሬክተሩ/ተወካይ፣DSSEM፣ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ከሌሎች የህግ አስከባሪ ኦፊሰሮች ጋር ከተማከሩ በኋላ አግባብነት ያለው/የሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ የሚከተለውን ምላሽ ለመስጠት እና ምርመራ ለማድረግ ቀዳሚ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

a) የቃጠሎ አደጋ/ወንጀል (ሆን ተብሎ እና በተንኮል ተነሳስቶ የተለኮሰ እሳት/) ወይም ለማቃጠል በቃል ወይም በጽሁፍ የተደረገ ዛቻ ማስፈራራት።

b) አውዳሚ መሳሪያ ማምረት ወይም መያዝ—ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ፣ ወይም መርዛማ ቁሶችን ማስተላለፍ ወይም ከሚያፈነዳ መሳሪያ ጋር ተጣምሮ ወይም ይህን ለማድረግ

---

[1] ሙሉ ርዕስ፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ስለሚፈጠሩ አደጋዎች/ክስተቶች ምላሽ በሚመለከት፥የህግ አስከባሪዎችን ጣልቃ ገብነት የሚያካትቱ ክስተቶችን ሪፖርት የማድረግ ፕሮቶኮሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ እንዲሁም የሌሎች ኤጀንሲዎች የማህበረሰብ ተሳትፎ ኦፊሰር ፕሮግራም እና ሌሎች የህግ አስፈፃሚዎችን በሚመለከት ኤፕሪል 4፣ 2022 የመግባቢያ ስምምነት ላይ ተቀምጠዋል። (የመግባቢያ ሠነድ)

የተዘጋጀ ተግባር (በተጨማሪ MCPS ደንብ EKA-RA፣ አደጋ እና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት ይመልከቱ)።

c) ስለቦታው ወይም የሚጎዳ መሣሪያ ማፈንዳትን እያወቁ/ሆን ተብሎ የሀሰት ሪፖርት ማቅረብ።

d) የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግበት አደገኛ እፅ ማሰራጨት ወይም ማምረት።

e) ከትምህርት ቤቱ የጤና ክፍል ውጭ የሕክምና ክትትል የሚያስፈልገው በሌላ ግለሰብ/ግለሰቦች ላይ የሚደርስ አካላዊ ጥቃትን በተመለከተ የሚደረግ 911 ጥሪ (የተጠረጠረ የሕፃናት ጥቃት እና/ወይም ቸልተኝነት፣ MCPS ደንብ JHC-RA ይመልከቱ፣ የሕፃናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ)

f) ስርቆት (የተሰረቀው ንብረት ዋጋ $1500 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በአንድ ተመሳሳይ ወንጀለኛ የተፈጸመ የአንድ ጊዜ ክስተት ወይም ተከታታይ ክስተቶች)።

g) ለማስፈራራት ወይም ጉዳት ለማድረስ ጥቅም ላይ የሚውል በትምህርት ቤት ንብረት ላይ አደገኛ ወይም ገዳይ መሣሪያ ይዞ መገኘት።[2]

h) ቁጥጥር የሚደረግበት አደገኛ ንጥረ ነገር ማሰራጨት እና/ወይም ይዞ መገኘት (በተጨማሪ የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ አልኮልን፣ ትምባሆ እና ሌሎች አደንዛዥ እፅ አላግባብ መጠቀምን መከላከል እና MCPS ደንብ IGO-RA ይመልከቱ፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ የአልኮል፣ የትምባሆ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ የመጠቀም ክስተት መመሪያ)።

(1) የሕግ አስከባሪ አካላት በምርመራው ውስጥ ግንባር ቀደም ይሁኑ/አይሁኑ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ነው ብለው የጠረጠሩትን ማንኛውንም ነገር ከያዙ በኋላ ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ማስረከብ አለባቸው።

(2) ነገር ግን፤ ከተማሪው(ዋ) ላይ ማቴሪያሉ የተገኘው ስለመዳኒት አጠቃቀም የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ኮንፈረንስ ወይም ኢንፎርሜሽን በሚጠየቅበት/በምትጠየቅበት ወቅት ከሆነ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ ስለተማሪው(ዋ) ማንነት በሚስጥር መጠበቅ እንዳለበ(ባ)ት የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል (MCPS ደንብ IGO-RA ይመልከቱ፡- "ተማሪዎች የተሳተፉበት የአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ እፅ መድሃኒቶች መጥፎ አጠቃቀም የመቆጣጠር መመሪያ)።

C. በት/ቤት ውስጥ የሚከሰቱ አስቸኳይ ያልሆኑ ሁኔታዎችን፣ ህግ አስከባሪዎች እና MCPS ተባብረው የተሻለውን የእርምጃ አካሄድ ለመወሰን ይሞክራሉ። አብዛኛዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈጠሩ ክስተቶች ያሉትን የትምህርት ቤት መገልገያዎች ለመጠቀም ይችላሉ። MOU-CEO ምላሽ ላልተሰጣቸው ሁኔታዎች፣ ት/ቤቱ ወደ ፖሊስ ከማስተላለፉ በፊት ተፈጻሚነት ያላቸውን፣ ነባር፣ አጠቃላይ የት/ቤት አገልግሎትን መጠቀም ይጠበቅበታል።

D. የሚከተሉት የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ጥሪዎች ወይም ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ምንም

[2] የቅቤ መቀቢያ ቢላዋ አደገኛ ወይም ገዳይ መሣሪያ አይደለም። In re Melanie H.፣ 120 Md.App.158 (1999) ይመልከቱ፡-

እንኳን ስለ ክስተቱ ሁሉም እውነታዎች ገና ያልተሰበሰቡ ቢሆኑም በአንድ ሰዓት ውስጥ ወደ "DSSEM" ማሳወቅ አለባቸው። እንደዚህ አይነት ክስተቶች እንደአስፈላጊነቱ ለህግ አስፈፃሚዎች ወይም ለሌሎች ኤጀንሲዎች አንድ በአንድ/እንደ ጉዳዩ ባህርይ መሰረት ተጨማሪ ሪፖርት ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡-

1. የደህንነት ክስተቶች

    a) ማንኛውም እሳት አደጋን ለመታደግ የሚቀርብ ጥያቄ (በተጨማሪ MCPS ደንብ EBA-RA፣ ስለ እሳት አደጋ ደህንነት ይመልከቱ)።

    b) ከውስጥ መቆለፍ፣ አካባቢን መልቀቅ ወይም መጠለያ ማግኘት (በተጨማሪ MCPS ደንብ EKA-RA፣ አደጋ እና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት ይመልከቱ)።

    c) አደገኛ ቁሳቁሶች የሚያስከትሉት ክስተት (በተጨማሪ MCPS ደንብ EKA-RA፣ አደጋ እና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት ይመልከቱ)።

    d) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ማንኛውም ዓይነት አካላዊ ወይም ወረቀት ማሰር

2. አስቸኳይ የጤና እንክብካቤ

    a) ለድንገተኛ ጊዜ የሕክምና እርዳታ ማንኛውም ጥያቄ (በተጨማሪ MCPS ደንብ EBJ-RA፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለሚደረግ የድንገተኛ አደጋ እንክብካቤ እና የመጀመሪያ እርዳታ) ይመልከቱ፡-

    b) ከባድ የአካል ጉዳትን የሚያመጣ ማንኛውም ክስተት፣ የሞት አደጋ፣ ከፍተኛ የአካል ህመም፣ወይም ማንኛውንም የአካል ክፍል ወይም የአእምሮ ማሳት ወይም እክል ረዘም ያለ ወይም ግልጽ የአካል ጉድለትን የሚያስከትል ጉዳት ተብሎ ይገለጻል።

    c) ማንኛውም ድንገተኛ የጤና አጠባበቅ ችግር ሲከሰት በስቴት ወይም የፌደራል ሪፖርት መስፈርቶች (ለምሳሌ፡- ከአናፊላክሲስ/anaphylaxis ጋር በተያያዘ ምክንያት የሚሰጥ ኢፒንፍሪን፣ ኦፒዮይድ/opioid ከመጠን በላይ መውሰድ ምክንያት የሚሰጥ ናሎክሶን/naloxone፣ ደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋስያን፣ ወይም አውቶማቲክ የልብ ምት ማስተካከያ ማሽን/ዲፊብሪሌተር defibrillator መጠቀም) (በተጨማሪም MCPS ደንብ JPD-RB ይመልከቱ)፣ አናፊላክሲስ ላለባቸው ተማሪዎች የድንገተኛ/አደጋ ጊዜ እንክብካቤ፣ እና የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ አልኮልን፣ ትምባሆ እና ሌሎች እፅ አላግባብ መጠቀምን መከላከል።

E. ስለ ክስተቱ ሁሉም እውነታዎች ገና ያልተጠናቀሩ ቢሆኑም የሚከተሉት ክስተቶች በአንድ ሰዓት ውስጥ ወደ OSSWB ሪፖርት መደረግ አለባቸው። የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎት ሰጪዎች ከተጠሩ እነዚህን ክስተቶች በቀጥታ ወደ DSSEM ሪፖርት ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

1. ማንኛውም የተማሪ እና/ወይም ከተማሪ የተያዘ ንብረት ፍተሻ እና መውረስ (በተጨማሪ MCPS ደንብ JGB-RA፣ ፍተሻ እና መውረስ ይመልከቱ)።

2. ሰክሽን IV.B.7 ላይ እንደተገለጸው SSE ተግባራቸውን በሚያከናውንበት ወቅት በትምህርት ቤት የደህንነት ጥበቃ ሰራተኛ (SSE) እና በተማሪ መካከል ሪፖርት ሊደረግ የሚችል የሃይል

አጠቃቀም።

3. የሚከተሉት የጤና ችግሮች፡-

   a) የተረጋገጡ ተላላፊ በሽታዎች (ለምሳሌ፡- ፐርቱሲስ/pertussis ወይም ሳንባ ነቀርሳ)

   b) ሌሎች ሪፖርት መደረግ ያለባቸው አደጋዎች በሜሪላንድ MCPS Regulation EBH-RA ተገልጸዋልበተማሪ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ሪፖርት ማድረግ/Reporting Student Accidents

      (1) በጭንቅላት፣ በአይን፣ በአንገት ወይም በአከርካሪ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳት።

      (2) እብጠትን የሚያስከትል ማንኛውም የአጥንት ወይም የመገጣጠሚያ ጉዳት።

      (3) ስፌት የሚያስፈልገው ማንኛውም የተወጋ ቁስል፣ መቃጠል ወይም መቁሰል።

      (4) ማንኛውም ጎጂ ወይም አግባብ ያልሆነ መድሃኒት መዋጥ፣ ኬሚካል ወይም ባዕድ ቁሳቁስ እና ማንኛውም ጉዳት የሚያስከትል የተከለከለ ንጥረ ነገር መዋጥ/መውጋት።

      (5) ማንኛውም የእንስሳት ንክሻ (በተጨማሪ የMCPS ደንብ EBK-RA ይመልከቱ፣ የእንስሳት ንክሻ ሪፖርት ማድረግ እና መንከባከብ)።

4. በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት/ብልሽት:

   a) የአስፈላጊ መሳሪያዎች፣ መገልገያዎች እና/ወይም አገልግሎቶች ጉልህ ወይም ወሳኝ ብልሽት፣ ወይም

   b) የትምህርት ቀን መቋረጥን የሚያስከትል ከባድ የንብረት ውድመት (በተጨማሪ MCPS ደንብ ECC-RA፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት ላይ የደረሰ ጥፋት ወይም ጉዳት ይመልከቱ)።

5. የስነምግባር ባህሪ ጣልቃ ገብነት፡-

   በታቀደው የትምህርት ቀን ላይ ከባድ የትምህርት መቋረጥን የሚያስከትል መጥፎ ምግባር።

## IV. ቅንጅት/ሲነርጂ እና ሌሎች የሪፖርት ፕሮቶኮሎች

A. ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር፣ በትምህርት ቀን ወይም በት/ቤት ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች የተከሰቱ ሁነቶች ወደ OSSWB ሪፖርት መደረግ ስላለበት እንደአግባቡ በሲነርጂ ተዘጋጅተው ይሰራጫሉ።

   1. ከርዕሰ መምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ ወይም ከ DSSEM ጥሪ ሲደርሰው OSSWB ሪፖርቱን ሲነርጂ/መረጃ ማስተላለፊያ ቋት ውስጥ በማስገባት እና ሲነርጂን በመጠቀም ከሌሎች ቢሮዎች ጋር ይገናኛል፤ማኔጅ ለማድረግና ስርዓት አቀፍ ምላሾችን አግባብነት ባላቸው ቢሮዎች መካከል ለማስተባበርና ለማቀናጀት ነገር ግን በዚህ ብቻ አይገደብም። ቢሮዎቹ እነዚህን ሁሉ ይመለከታል፡- "Risk Management; Office of Communications; the DSSEM (if the

contact did not originate from the DSSEM); the Office of Well-being, Learning and Achievement; Student Welfare and Compliance; the Office of the General Counsel (OGC), and the Department of Compliance and Investigations (DCI)"

2. ርእሰ መምህሩ/ዳይሬክተሩ/ተወካዩ (48 ሰአታት ውስጥ) የሲነርጂ ሪከርዱን ተጨማሪ መረጃዎችን በማካተት ሁሉም አስፈላጊ መረጃዎች ሲገቡ የክስተቱን ሪፖርት ያጠቃልላል/ይዘጋል።

B. የሚከተሉት ክስተቶች በስቴት ወይም በፌደራል መስፈርቶች ድንጋጌ መሠረት፣ MOU-CEO እና/ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሪፖርት የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው፣ OSSWB አንዳንዶቹን ክስተቶች በተጨማሪ ወይም በምትኩ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች ሪፖርት ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል።

1. የልጅ መጎሳቆል እና/ወይም ችላ መባል ሪፖርት መደረግ ያለበት፡- በ MCPS ደንብ JHC-RA ድንጋጌ መሠረትየልጅ ማጎሣቆልን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ ማካሄድ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች እና/ወይም ለጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎቶች ሪፖርት ይደረጋል።

2. የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች የአውቶቡስ አደጋዎችን በቀጥታ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የመጓጓዣ ዲፓርትመንት/MCPS Department of Transportation (DOT) ሪፖርት ያደርጋሉ። የአደጋ ስፍራ/ቦታ ኃላፊነት፣ ማሳወቅ፣ እና የሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች ከስቴትና ከፌዴራል መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው እና በ MCPS ደንብ EEA-RA፣ ስለ ተማሪ ትራንስፖርት የሚለው ላይ የተዘረዘሩ ናቸው። የአውቶቡስ አደጋ ወይም ሌላ በተሳፋሪ ላይ የደረሰ አደጋ ከሆነ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር መነጋገር በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ት/ቤቱ ስለ ክስተቱ ሪፖርት ከትራንስፖርት ክፍሉ (DOT) ከደረሰው በኋላ ወዲያውኑ ወደ OSSWB መደወል አለበት።

3. አንድ የሥራ ባልደረባ በተማሪ ላይ ስለሚፈጸም ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ እና ወከባ፣ በተማሪ ላይ የተፈጸመ ጾታዊ ጥቃት ጭምር ሪፖርት እንዳገኘ(ች) መረጃው/ኢንፎርሜሽኑ ወዲያዉኑ በ MCPS ቅጽ 230-35 ተቀናብሮ ለርእሰመምህር/ተወካይ ሪፖርት መደረግ አለበትስለ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራሪያ ሪፖርት ቅጽእና እንደሚከተለው ምርመራ ይካሄዳል፡-

   a) ከጾታዊ ጥቃት ሌላ፣ በተማሪዎች ላይ ጉልበተኝነት/ወከባ/ማስፈራራት በ MCPS Regulation JHF-RA በተደነገገው መሠረት በዶኩመንት ተይዞ በርእሰመምህር(ት) አማካይነት ምርመራ ይደረጋል በተማሪዎች ላይ የሚፈጸም ጉልበተኝነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት።

      (1) ክስተቱ Synergy (የመረጃ ማስተላለፊያ ቋት) ውስጥ ይመዘገባል።

      (2) ክስተቱ ሰክሽን III.B እና/ወይም III.C ላይ የተገለጹትን መስፈርቶች ካላሟላ በስተቀር ወደ OSSWB መደወል ወይም በሲነርጂ (የመረጃ ቋት) ውስጥ ሁኔታውን መመዝገብ አስፈላጊ አይሆንም። ትምህርት ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ መመሪያ ለማግኘት OSSWB ጋር እንዲማከሩ ያስፈልጋል።

   b) ስለ ተማሪ ፆታዊ ብልግና እና ጾታዊ ትንኮሳ በሚመለከት በቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ጾታዊ በደል እና ጾታዊ ትንኮሳ ውስጥ ተገልጿል፣ MCPS Regulation JHF-RA፣ ላይ በተገለጸው መሠረት ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ መደረግ አለበት።

ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራት፣ MCPS ደንብ ACF-RA፣ Title IX ምርመራ MCPS የተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳ። አንዳንድ ፆታዊ የትንኮሳ ዓይነቶች የወንጀል ድርጊት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይህም የወንጀል ቅጣትን የሚያስከትል ወይም የልጅ መጎሳቆል ሊሆን ይችላል፣ ስለሆነም MCPS ደንብ JHC-RA መሠረት የህጻናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ ፣ ለህግ አስከባሪ አካላት ምርመራ ወይም ሪፖርት ማድረግ ይጠይቃል እና/ወይም MOU-CEO ድንጋጌዎችን ይመልከቱ።

(1) ማንኛቸውም አግባብነት ያላቸው የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ ወደ OSSWB ይደውላሉ፣ ጥሪው እንደአግባቡ በተማሪ ደህንነት እና ሥነ ስርዓት ማስከበር ክፍል በሲነርጂ (የመረጃ ቋት) ላይ ተመዝግቦ ይሠራጫል። OSSWB ጋር በመተባበር፣ የተማሪ ደህንነት እና ደንብ አስከባሪ ክፍል MCPS የተማሪዎችን ፆታዊ ትንኮሳ ክስተቶች ሪፖርት ከተደረገ በኋላ የሚወሰደውን እርምጃና ምላሽ የመከታተል ሃላፊነት አለበት።

(2) የሕግ አስከባሪ አካላት ከተሳተፉ፣ MCPS የሚሰጠውን ምላሽ ከህግ አስከባሪዎች ጋር ለማስተባበር የተማሪ ደህንነት ጥበቃ እና ስነ ስርአት ማስከበር ክፍልን ማማከር አለበት። የተማሪ ደህንነት እና ስነ ስርአት ማስከበር ክፍል ከህግ አስከባሪዎች ጋር ተገቢው ቅንጅት መደረጉን ለ DSSEM ያሳውቃል።

(3) ክስተቱን በቦርድ ፖሊሲ ACF፣ "የተማሪዎች ፆታዊ ብልግና እና ጾታዊ ትንኮሳ" ላይ በተገለጸው መሰረት ርእሰመምህሩ/ተወካዩ ይመዘግባል። MCPS ደንብ JHF-RA፣ የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ ወይም MCPS Regulation ACF-RA፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Title IX ተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳና ምርመራ ሲነርጂ (የመረጃ ቋት) ውስጥ መመዝገብ።

4. ማንኛቸውም የአካል እንቅስቃሴን ማገድና መገደብ (MCPS ደንብ JGA-RA ይመልከቱ፣ የትምህርት ክፍል ማኔጅመንት እና የተማሪ ስነምግባር ባህሪ ጣልቃገብነት) ለልዩ ትምህርት ቢሮ ሪፖርት መደረግ እና ሲነርጂ (የመረጃ ቋት) ውስጥ መመዝገብ አለበት። 24 ሰዓት ውስጥ ለወላጅ/አሳዳጊ ማሳወቅ ያስፈልጋል።

a) በተጨማሪም፣ በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ ወላጅን/አሳዳጊን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት።

b) በማንኛውም የህዝብ ትምህርት ቤት በምንም ሁኔታ ማግለል/አግላይነት አይፈቀድም።

5. ሠራተኞች ወይም በጎ ፈቃደኞች ከሥራ ጋር የተያያዘ ጉዳት ሲደርስባቸው MCPS የሥራ ባልደረቦች በሥራ ላይ ለሚያጋጥም ጉዳት የማካካሻ ጥያቄዎችን የሚያስተዳድር ሦስተኛ ወገን ስለሆነ በቀጥታ ወደ CorVel ኮርፖሬሽን ሪፖርት መደረግ አለበት።

6. MCPS ደንብ ACA-RA፣ "መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ፣ እና የባህል ብቃት" በተቀመጠው የአፈጻፀም ሂደት መሰረት በስራ ቦታ ላይ የሚፈፀም ሰራተኞች የሚደርስባቸው ውንጀላ/ማስረጃ ያልቀረበበት ክስ እና ከሌሎች ሰራተኞች ጋር የተያያዙ ክሶች፣ ቅሬታዎች እና በስራ ቦታ ላይ የሚደርስ ጥቃት ሪፖርት ይደረጋል። MCPS ደንብ ACH-RA፣ በስራ ቦታ የሚፈፀም ጉልበተኝነት፣ MCPS ደንብ GKA-RA፣ አስተዳደራዊ ቅሬታ፣ ወይም ድርድር የተደረገባቸው ስምምነቶች።

7. MCPS መረጃን መሰብሰብ እና ለሜሪላንድ የትምህርት ቤቶች ደህንነት ማእከል (MCSS)/Maryland Center for School Safety (MCSS) ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፣ SSE እና በተማሪ መካከል SSE ተግባራቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ የሃይል ክስተቶች።

   a) ትምህርት ቤቶች SSE በተማሪ ላይ የተጠቀመባቸውን የሚከተሉትን የኃይል ዓይነቶች ማንኛውንም ክስተት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ትምህርት ቤቱ በፍጥነት ወደ OSSWB እና DCI የቃል ሪፖርት ማድረግ አለበት፣ከዚያም OSSWB በሲነርጂ (የመረጃ ማሰራጫ ቋት) የአደጋ ሪፖርት መረጃ ውስጥ ያስገባል። OSSWB ሪፖርቱን ወደ DSSEM ይልካል/ያሳውቃል።

      (1) እጅን ተጠቅሞ በጥፊ ተማሪን መምታት።

      (2) ሆን ብሎ በጉልበት ተማሪን መሬት ላይ መነተት።

      (3) ለማነቅ መሞከር ወይም ሌላ ጠንካራ ክንድ መጠቀም።

      (4) የመተንፈስ ወይም የመግባቢያ ችሎታቸውን የሚገድብ ወይም በሌላ መልኩ ጭንቅላታቸው፣ አንገታቸው ወይም አካላቸው ላይ ጫና በሚፈጥር ቦታ ላይ ተማሪን በተጋለጠ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ማቆየት።

      (5) ተማሪን በእጅ፣ በጉልበት፣ ወይም በእግር፣ ወይም በማንኛውም ሌላ ነገር መምታት።

   b) DCI፣ OSSWB፣ እና DSSEM በመነጋገር የተከናወኑትን ድርጊቶች እና የጉዳዩን እውነታ ለመገምገም መደበኛ ምርመራ ያካሂዳል።

   c) የጉዳዩን እውነታነት ለማረጋገጥ ከሚቀርቡት ማስረጃዎች ያለውን ቪዲዮ መመልከት፣ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ እና ተገቢ ሪከርዶችን መገምገምን ሊያካትት ይችላል ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

   d) የጉዳዩን እውነታነት ለማወቅ ኃይልን መጠቀም ያስፈለገበትን ምክንያት ጭምር ያጣራል።

      (1) በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ ርእሰ መምህር፣ መምህር፣ SSE ወይም ሌላ የትምህርት ሥርአት ሰራተኞች በት/ቤት ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚደረግ ጉዞ ላይ ግጭትን ወይም አካላዊ ድብድብን ጨምሮ ግጭቱ በእነርሱ ፊት በተማሪዎችም ሆነ በሌሎች ግለሰቦች መካከል ቢሆን ጥቃትን ለመከላከል ምክንያታዊ እና አስፈላጊ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ።

      (2) ጥቃትን ለመከላከል፣ ስርዓትን ወደነበረበት ለመመለስ እና የተፋላሚዎችን እና በአካባቢው ያሉ ግለሰቦችን ደህንነት ለመጠበቅ ጣልቃ ገብነት እና በተወሰነ ደረጃ ተመጣጣኝ ሃይል መጠቀም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

      (3) የሜሪላንድ ህግ በህጋዊ መንገድ ኃይል ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን የሚከተሉትን ዓላማዎች ያስቀምጣል።

(i) በአግባቡ የተተገበሩ የሰውነት እገዳዎች፣ MCPS ደንብ JGA-RA፣ የመማሪያ ክፍል አስተዳደር እና የተማሪ ባህሪ ጣልቃገብነት ላይ በተገለጸው መሰረት ብቻ።

(ii) ተማሪውን ለማረጋጋት ወይም ለማጽናናት ተማሪን ለአጭር ጊዜ ይዞ ማቆየት።

(iii) በአካል ማጀብ፣ ለጊዜው እጅን መያዝ፣ የእጅ መዳፍ/አንጓ፣ ክንድ ወይም እጅን፣ ክንድን፣ ትከሻን ወይም ጀርባን በመያዝ ተማሪን ወደ ደህና ቦታ እንዲራመድ መሸኘት (ማለትም፦ በአካል ማጀብ የተራዘመ ጊዜ የሚወስድ ስላልሆነ የተማሪውን በነፃነት የመንቀሳቀስ ችሎታ አይገድበውም)።

(iv) እንደ ምክር ያሉ ሌሎች የማስታገስ ዘዴዎች ካልተሳኩ አካባቢውን ለቆ ለመሄድ ፈቃደኛ ያልሆነ(ች) ተማሪን ከቦታው ማንቀሳቀስ።

(v) ተማሪዎችን ለመለያየት በሚደረገው መገላገል ውስጥ ጣልቃ መግባት።

e) DCI ምርመራው ድርጊቶቹ ምክንያታዊ እንዳልሆኑ ካረጋገጠ ወይም ይበልጥ ተገቢ፣ ምክንያታዊ አማራጮች ካሉ፣ MCSS በሪፖርት አቀራረብ ሂደቶች መሰረት DCI ድርጊቶቹን ለ፦MCSS ያሳውቃል።

C. የትምህርት ቀን መስተጓጎልን ለማያስከትል (ጥፋትን ሳይጨምር) የንብረት ብልሽት ወደ OSSWB ጥሪ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም፥ ነገር ግን በአምስት ቀናት ውስጥ በትምህርት ቤቱ ሲነርጂ መመዝገብ አለበት። ንብረት የማበላሸት/የማውደም ተግባር፡ ቫንዳሊዝም ከታወቀ በኋላ በአንድ ሰአት ውስጥ ወደ DSSEM እና OSSWB ሪፖርት ማድረግ እና በሲነርጂ መመዝገብ አለበት።

D. በትምህርት ዓመቱ በየጊዜው OSSWB ከሌሎች ቢሮዎች ጋር በመተባበር፣ ትክክለኛ ሪፖርት መደረጉን ለማረጋገጥ ሁሉም ክስተቶች በተሟላ ሁኔታ ሪፖርት መደረጋቸውን ያረጋግጣል።

V. **ኮሙኒኬሽን**

OSSWB ጉዳዩን በሚመለከት እንደአስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤቱ እና ከማህበረሰቡ ጋር የመገናኘት ሀላፊነቶችን የኮሚዩኒኬሽን ዲፓርትመንትን፣ DSSEM፣ DCI እና OGC ጨምሮ ለሚመለከታቸው ቢሮዎች ያሳውቃል እና ይተባበራል።

A. በተቻለ ፍጥነት፣ ርእሰ መምህሩ/ዳይሬክተሩ፣ OSSWB እና መተባበር ያለባቸው ቢሮዎች-

1. ተገቢውን የኮሙኒኬሽን መሪ መለየት (ማለትም ርእሰመምህር/ዳይሬክተር ሊሆን ይችላል)፣

2. ቁልፍ እውነታዎችን ለይተው ያረጋግጣሉ፣ እና

3. በሕግ አስከባሪ አካላት ወይም በሌሎች ኤጀንሲዎች በሚደረጉ ንቁ ምርመራዎች ላይ ጣልቃ ላለመግባት መከተል ያለባቸውን ሂደቶች መወሰን እና የተሳተፉትን ሰዎች ማንነት በምስጢር መጠበቅ፣ ይኼውም የግል እና የፍትህ ሂደት መብቶችን መጠበቅ፣ ከሰራተኛ ማህበራት ጋር

ድርድር የተደረጉ ስምምነቶችን እና ተፈጻሚነት ያላቸውን የመግባቢያ ስምምነቶች ማክበርን ይጨምራል።

B. ህግ አስከባሪ አካላት በአንድ ክስተት ውስጥ ሲሳተፉ፣ መረጃ የሚለቀቀው DCI እና OGC በመተባበር እንደአግባቡ OSSWB ሲፈቅድ ብቻ ነው።

C. ከልጆች በደል እና/ወይም ቸልተኝነት ጋር የተዛመዱ ክስተቶችን የሚመለከቱ ግንኙነቶች በ MCPS ደንብ JHC-RA፣ የሕፃናት በደል እና ችላ ማለትን ሪፖርት ማድረግ እና መመርመር ፣ እና የ MOU-CEO መሆን አለባቸው።

D. እንደአስፈላጊነቱ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች፣ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት መረጃን ከመስጠትዎ በፊት ከኮሙኒኬሽን ኃላፊ ጋር የሚደረግ ምክክር ያስፈልጋል።

E. አንድ ክስተትን በተመለከተ የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ የሚከተሉትን ነገሮች ሊያካትት ይችላል፦

1. ስለተፈጠረው ክስተት እና ችግሩን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች ዝርዝር

2. ወላጆች/አሳዳጊዎች እና/ወይም የቅርብ ተቆጣጣሪዎች ወይም ሌሎች ሊሰጡ የሚችሉት የድጋፍ ተግባራት/እንቅስቃሴዎች መግለጫ (እንደአስፈላጊነቱ)

F. ማንኛውም ለህዝብ ይፋ የተደረገ የግንኙነት መረጃ OSSWB በፋይል ውስጥ እና በሲነርጂ የመረጃ ቋት ውስጥ ይቀመጣል።

**ተዛማጅ ምንጮች፦** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-307(a) and §7 1508; Code of Maryland Regulations §13a.08.01.12 and §13A.08.04.02.B(11)(b); and Maryland State Department of Education, Maryland Guidelines for a State Code of Discipline (2014).

**የዚህ ደንብ ታሪክ፦** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 285-9 ኖቬምበር 19, 1976። ጃኑዋሪ 31, 1992 ተሻሻለ፣ ኖቬምበር 4, 1996 ተሻሻለ፣ ጁላይ 20, 1998 ተሻሻለ፣ ሴፕቴምበር 24, 1999 ተሻሻለ፣ የቢሮው መጠሪያ የተለወጠው ጁን 1, 2000፣ ፌብሩዋሪ 28, 2006 ተሻሻለ፣ ኦክቶበር 18, 2013 ተሻሻለ፣ ሴፕቴምበር 5, 2014 ተሻሻለ፣ ሴፕቴምበር 5, 2018 ተሻሻለ፣ዲሴምበር 17, 2018 ተሻሻለ፣ኦገስት 31, 2021 ተሻሻለ፣ፌብሩዋሪ 1, 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><th>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</th><th>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</th></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org